*ለ ኢሕአፓ የሃገር እናድን ጥሪ ፈጣን ባጎ ምላሽ መስጠት የዜግነት ግዴታችን ነው*

*አበባው ተክለብርሃን ኖርዌይ ኦስሎ ከተማ*

እናት ሀገራችን ኢትዮጵያ የሰው ዘር መገኛና ለዘመናት ጥቁር ሕዝብን የሚያኮራ ቅኝ ገዥዎችን ያሳፈረ የአድዋ ድል ባለቤት የሆነችና የሁላችንም የኢትዮጵያውያን መኩሪያ የሆነች ሃገር ናት። ሆኖም ግን ለዘመናት በሃገሪቱ የስልጣን መንበር ላይ እየተፈራረቁ ሃገሪቱን ለባሰ ድህነት የዘፈቁ የፊውዳሉ ስርዐት አራማጆች፣ የፋሽስቱ የደርግ ስርዐት፣እንዲሁም አሁን ሀገሪቷን በዘርና በሃይማኖት እየከፋፈለ ኢትዮጵያውያንን ለውርደትና ለስደት የዳረገ ዘረኛውና አምባገነኑ የወያኔ ቡድን ይህን አኩሪ ታሪኳን ጥላሸት ሲቀቡ ኖረዋል።

ከዛሬ 40 ዓመታት በፊት በሰፊው ሕዝብና በኢትዮጵያውያን ወጣቶች ትግልና መስዋዕትነት የተመሰረተው ኢሕአፓ ለአገራችንና ለሕዝባችን የተሻለ ራዕይና ዓላማ አንግቦ ከኢትዮጵያዊነት ጋር ከሚጣሉት ሁሉ ጋር እየተጣላ በደም የተጻፈ ታሪክ ያስመዘገበ ለዘመናት ከውጭና ከውስጥ ከጸረ ኢትዮጵያ ሃይሎች ከጠባብ ብሄርተኞቹ እንደ ወያኔ ሻቢያ እና ኦነግ መስሎቹና ከፈሽስቶቹ ደርጎች ጋር ይህ ቀረሽ ያማይባል ለአገሩ ኢትዮጵያ መክፈል ያለብት የመጨረሻውን ውድ ሕይውቱን ሰጥቷል እየሰጠም ይገኛል። የነዚህን ጸረ ኢትዮጵያ ሃይሎች ማንነት ሲያጋልጥና ሲታገል ኖሯል አሁንም የትግሉ ነው ሕይወቴ በማለት አገራችንን እናድን እያለን ነው።

እነሆ እኔም ዛሬ ኢትዮጵያውያንና ሃገር ወዳድ የሆኑ ወገኖችን በተለይ ወጣቶችን አርድ አንቀጥቅጥ ለሆነ ጸረ ወያኔ ሕዝባዊ ትግል መረባረብ አለብን ብየ ለጥሪውም ፈጣንና በጎ ምላሽ መስጠት አለብን ብየ አምናለሁ።

በኢሕአፓ የቀረበውን የሃገርን እናድን እንቅስቃሴ እንዲጠናከር ፍሬ እንዲያፈራ በውስጥም በውጭውም ተጨባጭ የሕዝብ ድጋፍ አስፈላጊ ለመሆኑ ምንም አያጠያይቅም። ከዚህ አኳያ በተለይ በውጭ ነዋሪ የሆነው ኢትዮጵያውያን ልናበረክት የምንችለው አስተዋጸኦ ከፍተኛ ነውና ለዚህ ክቡር ዓላማ መረባረቡ የወቅቱ ሁነኛ አጀንዳ መሆን አለበት።

ስለሆነም ዛሬ ሁሉንም ሀገር ወዳድ የሆኑና በኢትዮጵያዊነት ላይ የማይደራደሩ ወገኖችን የወያኔውን ቡድን ከስልጣን ለማውረድና ለመገርሰስ የኢሕአፓን የሀገር አድን ጥሪን መደገፍና በጎና ፈጣን ምላሽ መስጠት አለብን ብየ ከመምንባቸው ከብዙዋቹ ነገሮች ጥቂት ምክንያቶች ብቻ እንዳነሳ ፍቀዱልኝ እንድያው ታጡታላቹት ብየ ሳይሆን ለማስታውስ ያህል፡

1ኛ፡- ከመሰረቱ የወያኔው ቡድን ሲቋቋም ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያውነትን ለማጥፋት የተነሳ ቡድን በመሆኑ የመገንጠል ዓላማና ፕሮግራም ሲያራምድ የነበረና አሁንም የትግራይ ነጻ አውጪ እየተባለ እየተጠራ ያለ

እንኳን ለእኛ ለኢትዮጵያውን ለስንቶቹ የጥቁር ሕዝቦች የነጻነት ተምሳሌ የሆነውን ሰንደቅ ዓላምችንን ብጣሽ ጨርቅ በማለት ከራሱ ሕዝብ ከታሪክ ማንነትና ዕምነት ጋር የተጣላ በመሆኑ ገና ከመሠረቱ ከኢትዮጵያዊነት ጋር የማይታረቅና የማይቀራረብ መስረታዊ ችግር ያለበት በመሆኑ

2ኛ፡- ኢትዮጵያን የባሕር በር ከማሳጣት አንስቶ ዛሬ የሃገሪቷን መሬቶች ለአረብ ሀገር ካፒታሊስቶች፤ ለእስያ ከበርቴዎች፤ ለሱዳንና ለሌሎች ባዕዳን አሳልፎ እየሰጠ፤ በተለይ የወገናቸው ስቃይና እርዛት ምንም ስሜት ለማይሰጣቸው ሆድአደር የሃገር ውስጥ ከበርቴዎች በመቸብቸብና የሀገሪቷንና የሕዝቡን ዕጣ ፈንታ ለዘመናት ወደ ማያበቃ ቀውስ ውስጥ እየከተተ በመሆኑ

3ኛ፡- የሀገሪቷን የደሕንነት፤የመከላከያ፤የኢኮኖሚ አውታሮችን፤በተለይ ከሁሉ በላይ የሕዝብ የሆነውን የሃገሪቱን ስልጣን በተጭበረበረ ምርጫና በመሳሪያ ሃይል በመንጠቅና የአንድ ብሄር የበላይነት እንዲነግስበት በማድረግ ሌላው ኢትዮጵያዊ በገዛ ሃገሩ ባይተዋር መሆኑና ለከፍተኛ የኑሮ አዘቅት በመዳረጉ

4ኛ፡- በሀገሪቷ ውስጥ የሚገኙ የውጭና የሃገር ውስጥ ንግዱን የወያኔ ባለስልጣናት እራሳቸው በሚያሳፍር መልኩ በሞኖፖል የተቆጣጠሩት ከመሆኑም በተጨማሪ የማስሚዲያ ነጻነት፤በፖለቲካ ፓርቲ የመደራጀትና ሕዝቡ አማራጭ መረጃ የማያገኝበት፤በነጻነት ሃሳብን የመግላጽ መብት የታገደበትና ወጣቱ በሀገሩ ጉዳይ ተስፋ እንዲቆርጥና ስደት እንደ አማራጭ ሆኖ ሃገሩን ለቆ እየወጣ በባሕርና በየበረሃው ለአሰቃቂ አሟሟትና እንግልት እየዳረገ በመሆኑ

5ኛ፡- ወያኔ እራሱ የጻፈውን የይስሙላ ሕገ መንግስት እንኳን የማያከብር እብሪተኛ ቡድን ነው። ለምሳሌ ለዘመናት ተከባብረው በኖሩ የክርስትናና የእስልምና እምነት ተከታዮች መሃል አለመተማመን ለመፍጠርና በሃይማኖቶች መሃል ጣልቃ በመግባት ድምጻችን ይሰማ የዕምነት መሪዎቻችንን እንምረጥ ያሉ ሙስሊም ወገኖቻችንን በማሰር፤የዋልድባ ገዳምን በማረስና በኦርቶዶክስ የእምነት ቀኖና ውስጥ ጣልቃ በመግባት ዜጎችን የእምነት ነጻነት በመከልከሉ

6ኛ፡- በአንድና በሌላ ብሄር ላይ ያነጣጠረ ዘር የማጥፋት እርምጃ በሃገሪቱ ውስጥ የዕለት ተዕለት ትዕይንት እየሆነ በመምጣቱ፡- ለምሳሌ የአማራ ብሄር ተወላጆችን ለዘመናት ከሌላው ብሄር ጋር በአብሮነት ከኖሩበት ቀዩ በማፈናቀል አረጋውያን፤ሴቶች፤ሕጻናት ለእንግልትና ለሞት እየዳረገ በመሆኑ፤አንዱን ብሄር ከሌላው ብሄር ጋር በማጋጨት ሀገሪቷን ለ 22 ዓመታት ሲጨቁነና ሲረግጥ በመኖሩ

7ኛ፡-ዛሬ የሀገሪቱ የጀርባ አጥንት የሆነውና ሀገር ተረካቢው ወጣት የፈጠራ ባለቤትነቱን እየተነጠቀና በሰለጠነበት የሙያ መስክ ለመሰማራት ከዕውቀት ይልቅ ወያኔነት እንደመስፈርት እየታየ፤በግድ የወያኔ አባል ካልሆንክ እየተባለ የኑሮ አዘቅት ውስጥ እየተዘፈቀና የወያኔ ተለጣፊ እየሆነ፤እምቢ አሻፈረኝ ካለ ደግሞ እየታፈነና እየታሰረ እየተገደለ በሀገሩ ተስፋ እንዲቆርጥና፤በአባይ እንገድብልሃለን የማይጨበጥ ተስፋ እየተደናገረ ፤ አለመተማመንና ግለኝነት ሰፍኖ ይኸው ለስደትና ለእንግልት ወጣቱ ትውልድ እየተዳረገ በመሆኑ

እነዚህና ሌሎች ተቆጥረው የማይዘለቁ ግፍና በደል በሃገሪቷ ላይ ለ 22 ዓመታት ሲፈጸም ቆይቷል።ይህን ሀገሪቷን ተብትቦ የያዛትን የወያኔ አምባገነን ቡድንና ሥርዓት ለመገርሰስና ከስሩ መንግሎ ለመጣል፤ሕዝባችንን ከሥቃይና ከሞት ለመታደግ፤ የኢሕአፓን የሀገር እናድን ጥሪውን ተቀብሎ አገራችንን ማዳን የግድ ይላል።

ወያኔ በአማራ ሕዝብና ተወላጆች ላይ በሚካሄደው የዘር ማጥፋትና ማፈናቀል ወንጀል ተጠያቂ ነው!!

የሙስሊም መፍትሄ አፈላላጊ ኮሚቴዎች በአስቸኳይ ይፈቱ!!

ሀገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን እነሆ ተነሱ!!

ትግሉን አቀጣጥሉ!!

ሞት ለወያኔና ለጀሌዎቹ!!

ድል ለኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ!!

እናቸንፋለን!!

***አበባው ተክለብርሃን ኖርዌይ ኦስሎ ከተማ***